**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን**

# በኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለሚሰሩ የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጥበት እና ከውጭ አገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር እውቀት እና ክህሎት አፈፃፀምን ለመምራት የወጣ መመሪያ ቁጥር ፯፻፷፪/፳፻፲፬

**Ethiopian Investment Commission**

# A Directive Regulating the Issuance of Work Permit to Expats Employed in Investments and the Implementation of Knowledge and Skill Transfer from Expats to Ethiopians

**ታህሳስ ፳፻፲፬ ዓ.ም**

**DECEMBER 2021**

**አዲስ አበባ**

**ADDIS ABABA**

| | |
|---|---|
| **በኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለሚሰሩ የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጥበት እና ከውጭ አገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር እውቀት እና ክህሎት አፈፃፀምን ለመምራት የወጣ መመሪያ** | **A Directive Regulating the Issuance of Work Permit to Expats Employed in Investments and the Implementation of Knowledge and Skill Transfer from Expats to Ethiopians** |
| በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፲፩ሺ፹/፪ሺ፲፪ አንቀፅ ፳፬(፩) ላይ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ፈቃድ ለሰጣቸው ባለሃብቶች የአንድ ማእከል አገልግሎት እንደሚሰጥ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች መንግስታዊ አካላትን እንደሚያስተባብር የተመለከተ በመሆኑ፤ | *Recognizing* that Article 24(1) of the Investment Proclamation No.1180/2020 has provided for Ethiopian Investment Commission to provide one stop services to investors it has issued investment permits and coordinate relevant agencies; |
| በኢንቨስትመንት ደንብ ቁ.፬፻፸፬/፳፻፲፪ አንቀፅ ፲፰ (፩)(መ) እና አንቀፅ ፲፱ መሰረት በአንድ ማዕከል አሰራር ማዕቀፍ ከሚሳለጡ አገልግሎቶች መካከል አንዱ እና ዋናው የውጭ አገር ሰራተኞች ቅጥር፤ የስራ ፈቃድ አሰጣጥ እና ከውጭ አገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር እውቀት እና ክህሎትን የሚመለከት በመሆኑ፤ | *Whereas* under Article 18(1)(d) and Article 19 of the Investment Regulation No.474/2020, one of the key functions facilitated in one stop service is the employment of expats, issuance of work permit, and the transfer of knowledge and skills from expats to Ethiopian employees; |
| ከውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ አሰጣጥ እና እውቀት ሽግግር ጋር በተያያዘ በየጊዜው ያጋጠሙ ክፍተቶች እና ውስንነቶችን ለማስቀረት በኢንቨስትመንት አዋጁ እና ደንቡ ላይ መሰረታዊ እና ገዢ የሆኑ መርሆች በተሻለ ዝርዝር የቀረቡ መሆኑን በመገንዘብ፤ | *Recognizing* that the Investment Proclamation and Investment Regulation have provided for basic and governing principles aimed at narrowing gaps and limitations encountered in the issuance of expat work permits and the transfer of knowledge and skills; |
| በተጨማሪም በኢንቨስትመንት አዋጁ አንቀፅ ፳፪(፯) እና ኢንቨስትመንት ደንቡ አንቀፅ ፲፱ ላይ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እና በመመካከር ከላይ የተመለከቱ ጉዳዮችን ዝርዝር አፈፃፀም የሚመራ መመሪያ እንዲያዘጋጅ እና ተፈፃሚ እንዲያደርግ የተደነገገ በመሆኑ፤ | *Realizing,* further, that under Article 22(7) of the Investment Proclamation and Article 19 of the Investment Regulation, it is provided the Ethiopian Investment Commission, in collaboration and consultation with the Ministry of Trade and Industry and the Ministry of Labor and Social Affairs, shall prepare and implement a directive regulating in detail matters stated herein above; |
| የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ አገር ዜጎች በተፈቀደላቸው የሥራ መስኮችና ድርጅቶች ውስጥ ብቻ ሕግና ሥርዓትን ተከትለው እየሰሩ መሆኑን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ተገቢው ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ የሚደረግበት የተጠናከረ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤ | *Understanding* that it is imperative to adopt a robust working procedure that allows the Commission, in collaboration and coordination with the relevant organs, to monitor, supervise and |
| የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኢንቨስትመንት አዋጁ አንቀጽ ፳፪ እና በኢንቨስትመንት ደንቡ አንቀፅ ፲፱ ላይ በተሰጠው | |

| | |
|---|---|
| ሥልጣን መሠረት ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እና በመመካከር ይህን የአሰራር መመሪያ አውጥቷል፡፡ | support whether expat employees issued with work permits are actually serving in authorized work positions and within the specified enterprises in compliance with the relevant rules and regulations;<br><br>*Now, therefore*, in accordance with the powers vested under Article 22 of the Investment Proclamation and Article 19 of the Investment Regulation, the Ethiopian Investment Commission, in collaboration with the Ministry of Trade and Industry and the Ministry of Labor and Social Affairs, has issued this Directive. |
| **ክፍል ፩**<br><br>**ጠቅላላ ድንጋጌዎች** | **PART 1**<br><br>**GENERAL PROVISIONS** |
| **፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**<br><br>ይህ መመሪያ "በኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለሚሰሩ የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የ ሚሰጥበት እና ከውጭ አገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር እውቀት እና ክህሎት አፈፃፀምን ለመምራት የወጣ መመሪያ መመሪያ ቁጥር **፯፻፸፪/፳፻፲፫**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ | **1. <u>SHORT TITLE</u>**<br><br>This Directive may be cited as "Directive Number 772/2021 A Directive Regulating the Issuance of Work Permit to Expats Employed in Investments and the Implementation of Knowledge and Skill Transfer from Expats to Ethiopians". |
| **፪. <u>ትርጓሜ</u>**<br><br>በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-<br>፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፲፩፻፹/፪፻፲፪ ነው፡፡<br>፪/ "ደንብ" ማለት የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፳፻፲፪ ነው፡፡<br>፫/ "ኮሚሽን" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ከሚሽን ማለት ነው፡፡<br>፬/ "የውጭ አገር ዜጋ" ማለት የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡<br>፭/ "የሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት" ማለት እንደአግባብነቱ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ለመሥራት የሥራ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ለሚቀርብላቸው የውጭ አገር ዜጎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ነው፡፡<br>፮/ "ተገቢ ሙያ" ማለት የውጭ አገር ዜጋው ለሚቀጠርበት | **2. <u>DEFINITION</u>**<br><br>In this Directive,<br>1/ "Proclamation" means the Investment Proclamation No.1180/2020.<br>2/ "Regulation" means the Investment Regulation No.474/2020.<br>3/ "Commission" means the Ethiopian Investment Commission.<br>4/ "Foreign Citizen" means any person who is not a citizen of Ethiopia.<br>5/ "Concerned Government Office" shall, as appropriate, mean a government organ that issues a certificate of competence to foreigners on whose behalf an application has been submitted for the issuance of work permit to work in the country. |

| | |
|---|---|
| የሥራ መደብ ሙያዊ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰጠው ሕጋዊ የትምህርት እና የሥልጠና ማስረጃ ወይም የሥራ ልምድ ማለት ነው።<br>፯/ “ተተኪ ሠራተኛ” ማለት የውጭ አገር ዜጋ በተመደበበት የሥራ መደብ ላይ በሰልጣኝነት ተመድቦ የውጭ አገር ዜጋውን ለመተካት ዕውቀት እና ክህሎት የሚቀስም ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ማለት ነው።<br>፰/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው።<br>፱/ በዚህ መመሪያ የተቀመጠ የወንድ ጾታ አገላለጽ ለሴትም ያገለግላል።<br>፲/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላት እና ሐረጎች በአዋጁ፣ በደንቡ እና በሰራተኛ እና አሰሪ አዋጅ ቁጥር ፲፩፻፶፮/፳፻፲፩ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። | 6/ “Relevant Profession” means educational and training document or certificate of service legally issued to the expat and attesting professional competence to engage in specific work position.<br>7/ “Replacement Employee” means an Ethiopian employee assigned as trainee to acquire the necessary knowledge and skill and replace the expat employee.<br>8/ “Person” means a natural person or juridical person.<br>9/ Any gender expression in the masculine includes the feminine.<br>10/ All other words and phrases referred to in this Directive shall have the meaning assigned to them under the Proclamation, Regulation and the Labor Proclamation No.1156/2019. |
| **፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**<br>፩/ ይህ መመሪያ በኮሚሽኑ አስተዳደር ስር በሚወድቁ ኢንቨስትመንቶች ማለትም፡<br>ሀ) ሙሉ በሙሉ በውጭ ባለሀብት በተያዘ ኢንቨስትመንት፤<br>ለ) በአገር ውስጥ እና በውጭ ባለሀብቶች በጋራ በተያዘ ኢንቨስትመንት፤<br>ሐ) በአዋጁ እንደ የአገር ውስጥ ባለሀብት በተቆጠረ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ባልሆነ የውጭ አገር ዜጋ በሚካሄድ ኢንቨስትመንት፤<br>መ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት የኢንቨስትመንት መስክ አግባብ ካለው የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት ባለበት የአገር ውስጥ ባለሀብት በሚካሄድ ኢንቨስትመንቶች፡<br>በሚቀጠሩ የውጭ አገር ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።<br>፪/ ይህ መመሪያ - በስደተኞች አዋጅ ቁጥር ፲፩፻፲/፳፻፲፩ አንቀፅ ፳፮ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስትና አለም አቀፉ ማህበረሰብ በጋራ በሚቀርጿቸው - ኢትየጵያውያን እና ስደተኞችን በጋራ በሚያሳትፉ የገጠርና የከተማ ኢንቨስትመንት መስኮች ውጭ ባሉ የስራ እድሎች በሚቀጠሩ - የፀና የስደተኛ መታወቂያ በያዙ ስደተኞች ላይ - በተመሰሳይ ተፈፃሚ ይሆናል። ሆኖም በአመልካቾች አንፃር ከፓስፖርት፤ መግቢያ ቪዛ እና የአገልግሎት | **3. <u>SCOPE OF APPLICATION</u>**<br>1/ This Directive shall regulate expat employees waged in investments whose administration fall within the mandate of the Commission, namely:<br>a) Wholly foreign owned investment;<br>b) Joint investment between domestic and foreign investors;<br>c) Investment of a foreign national, not Ethiopian by origin, who is treated as a domestic investor pursuant to the Proclamation.<br>d) Investment made by a domestic investor in areas eligible for incentives and required to obtain a business license from an appropriate federal organ.<br>2/ This Directive shall apply to recognized refugees who hold a valid identity paper and are engaged in waged employment, excluding refugees who, in accordance with Article 26 of the Refugees Proclamation No.1110/2019, are eligible to engage in rural and urban investment projects jointly designed by the Ethiopian government and the international community to benefit refugees and |

| | |
|---|---|
| ክፍያ ጋር በተያያዘ የተቀመጡ ሌሎች ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሟሉ አይጠበቅም።<br>፫/ ኮሚሽኑ አግባብነት ላላቸው ተቆጣጣሪ መንግስታዊ አካላት የሰጠውን ውክልና መሰረት በማድረግ - በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ወይም ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት አገልግሎት፣ እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት ፈቃድ በተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ድርጅቶች የሚቀጠሩ የውጭ አገር ዜጎች የስራ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከናወን ይሆናል።<br>፬/ በሌሎች ህጎች ላይ በተለየ ሁኔታ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና ፪ ላይ ከተዘረዘሩት ውጭ ባሉ ሁኔታዎች የሚቀጠሩ የውጭ አገር ሰራተኞች የሚስተናገዱበት አግባብ እና የሚገዙበት መርህ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።<br>፭/ ይህ መመሪያ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና ፪ በሚሸፈኑ ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጎች፣ በቀጣሪ ድርጅቶች፣ እንዲሁም መመሪያውን በሚተገብሩ ሌሎች የመንግሥት አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። | Ethiopian nationals. However, requirements established in connection with the submission of passport, entry visa and service charge shall not be met by a refugee applicant.<br>3/ The Ministry of Labor and Social Affairs shall continue to issue work permit for expats employed by investment enterprises licensed by the pertinent government organs in pursuance of powers delegated from the Commission and engaged in air transport services, electric power generation, or transmission or distribution services, and communication services.<br>4/ Without prejudice to otherwise stipulations under any laws, the treatment of expat employees that fall outside the scope of sub-articles 1-2 of this Article shall be regulated through the directive issued by the Ministry of Labor and Social Affairs.<br>5/ This Directive shall apply to expat employees and employers covered under sub-articles 1-2 of this Article, and other government organs that implement the Directive. |
| **ክፍል ፪**<br>**ስለ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም** | **PART 2**<br>**ISSUANCE AND USE OF WORK PERMIT** |
| **፬. <u>የሥራ ፈቃድ ማውጣት ስለማስፈለጉ</u>**<br>፩/ በዚህ መመሪያ የሚሸፈን ማንኛውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ ወይም ተገቢ ሙያ ያላቸውን በከፍተኛ ማኔጅመንት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአሰልጣኝነት፣ በቴክኒክ እና ሌሎች መሰል ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችን መቅጠር ይችላል።<br>፪/ ለኢንቨስትመንት አስፈላጊ ከሆነ እና ተገቢ ሙያ/ልምድ ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ኮሚሽኑ ለማንኛውም ባለሀብት ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለሚሰራ የውጭ ዜጋ የትዳር አጋር የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።<br>፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ በተመለከቱ የሥራ መደቦች ላይ የውጭ አገር ዜጎችን ቀጥሮ ማሰራት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት ከኮሚሽኑ የሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት። | **4. <u>REQUIREMENT OF OBTAINING WORK PERMIT</u>**<br>1/ Any investor covered by this Directive may employ required or duly qualified foreigners for positions of higher management, as supervisors, trainers, technical positions, and other related roles.<br>2/ The Commission may issue work permit to a cohabiting spouse of any investor or expat employee provided that the cohabiting spouse's pertinence and qualification for operation of an investment is ascertained.<br>3/ Any investor who intends to employ foreigners for positions specified under sub-article 1 of this Article must obtain work permit from the |

| | |
|---|---|
| | Commission. |
| **፭. <u>በከፍተኛ ማኔጅመንት የሚመደቡ የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ አሰጣጥ</u>**<br><br>፩/ ማንኛውም ባለሀብት እንደ አስፈላጊነቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚን (CEO)፣ ዋና የኦፐሬሽን ኃላፊን (COO)፡ ዋና የፋይናንስ ኃላፊን (CFO) እና የቦርድ ሊቀመንበርን ጨምሮ ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልጉ የውጭ ዜግነት ያላቸው ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላትን መቅጠር ይችላል።<br>፪/ ድርጅቱ በዚህ መልኩ የሚቀጥራቸው የማኔጅመንት አባላት ቁጥር፡<br>ሀ) በፕሮጀክት ግንባታ ምዕራፍ የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጅን ብቻ የሚያካትት ሲሆን፤<br>ለ) በትግበራ ምዕራፍ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ዋና ስራ አስኪያጅ፤ ምክትል ስራ አስኪያጅ፤ ዋና የኦፐሬሽን ኦፊሰር፤ ምክትል የኦፐሬሽን ኦፊሰር፤ የፋይናንስ ጉዳይ ሀላፊ፡ የገበያ ስራ አስኪያጅ እና እንዳግባብነቱ የቦርድ ሊቀመንበርን ብቻ የሚያካትት ይሆናል።<br>፫/ የድርጅት መዋቅር ያስቀመጠው የተለየ አስተዳደራዊ አደረጃጀት ቢኖርም እንኳ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪ ከተዘረዘሩት ወይም በባህሪያቸው ከነዚህ መደቦች ጋር በቀጥታ ተመዛዛኝ ከሆኑት ውጭ የሚመለከቱ የማኔጅመንት ሰራተኞች ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም እንደ ከፍተኛ ማኔጅመንት አይቆጠሩም።<br>፬/ የከፍተኛ ማኔጅመንት አባላት የሥራ ፈቃድ የውጭ ዜግነት ያላቸው ሌሎች ሠራተኞችን አስመልክቶ የወጡ ቅድመ-ሁኔታዎች በተለይም በኢትዮጵያውያን የሚሸፈኑ የስራ መስኮች ዝርዝር፤ እንዲሁም የስልጠና እና የእውቀት ሽግግር ግዴታዎችን መከተል ሳያስፈልግ ይሰጣል፤ በየዓመቱም በአሰሪ ድርጅቱ ጥያቄ ሲቀርብ ይታደሳል።<br>፭/ በትግበራ ምዕራፍ ላይ የሚገኝ ድርጅት ከአጠቃላይ የማኔጅመንት አባላቱ ቢያንስ ሲሶውን በኢትዮጵያውያን የሸፈነ እንደሆነ የውጭ ዜግነት ላላቸው የማኔጅመንት አባላቱ ባንድ ጊዜ የሚሰጠው የስራ ፈቃድ የሁለት አመት የአገልግሎት ጊዜ እንዲኖረው ኮሚሽኑ ይወስናል። | **5. <u>ISSUANCE OF WORK PERMIT FOR EXPATS EMPLOYED IN TOP MANAGEMENT POSITION</u>**<br><br>1/ Any investor may, as needed, employ foreigners for top management positions including Chief Executive Officer (CEO), Chief Operation Officer (COO), Chief Finance Officer (CFO) and Board Chairman.<br>2/ The number of management members employed by an enterprise shall accordingly be as follows: -<br>a) during project construction phase, the Project Manager and Deputy Project Manager;<br>b) during implementation phase, the Chief Executive Officer or General Manager, Deputy General Manager, Chief Operation Officer, Deputy Operation Officer, Chief Finance Officer, Marketing Manager, and as appropriate, the Board Chairman.<br>3/ A different organizational structure established by an enterprise notwithstanding, any other management employee so depicted by the enterprise who is not specifically covered under sub-article 2 above or other directly corresponding positions shall not be considered as top management for purposes of this Directive.<br>4/ The work permit of top management members shall be issued and renewed annually based on request submitted by the employer without the need for complying with preconditions set for other expats - particularly in relation to positions that can be filled by Ethiopians and duties pertaining to knowledge and skill transfer.<br>5/ The Commission shall decide to issue a work permit that is valid for two years in respect of expat employees of enterprise in implementations phase if the enterprise covers a third of its management |

| | |
|---|---|
| | members by Ethiopians. |
| **<u>፮. ከከፍተኛ ማኔጅመንት ውጭ ባሉ መደቦች የሚቀጠሩ የውጭ አገር ሰራተኞች ቁጥር ስለሚወሰንበት ሁኔታ</u>**<br><br>፩/ ማንኛውም ባለሀብት በድርጅቱ ውስጥ ለግንባታ ምዕራፍ፤ ለማሽን ተከላ፤ ለኦዲት እና ሂሳብ ስራ፤ ለሱፐርቪዥን፤ ለኮሚሽኒንግ ወይም ሙከራ ሥራ፤ ወይም በተቆጣጣሪነት፣ በአሰልጣኝነት፤ በጥገና እና ሌሎች የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችን ቀጥሮ ለማሰራት የሥራ ፈቃድ ማውጣት የሚችለው በሚከተለው አኳኋን ብቻ ነው፡፡<br><br>፪/ በፕሮጀክት ግንባታ ምዕራፍ፡<br><br>ሀ) የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጅን ሳይጨምር ድርጅቱ በፕሮጀክት ግንባታ ምዕራፍ የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ሰራተኞች ቁጥር ከኢትዮጵያውያን ቋሚ የፕሮጀክት ተቀጣሪዎች ቁጥር አንፃር ሲታይ ከ፲ በመቶ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡<br>ለ) ሆኖም ድርጅቱ ትርፉን ወይም ሌላ ካፒታል በመጠቀም ያለውን ኢንቨስትመንት በማሳደግ ወይም በማስፋፋት ስራዎች ላይ የተሰማራ እንደሆነ በግንባታ ሂደት የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ሰራተኞች ቁጥር ከኢትዮጵያውያን ተቀጣሪዎች ቁጥር አንፃር ሲታይ እስከ ፲፭ በመቶ ከፍ እንዲል ኮሚሽኑ ሊወስን ይችላል፡፡<br>ሐ) ድርጅቱ ከስር በአንቀፅ ፰ ላይ ከተመለከቱ ሰነዶች በተጨማሪ ከማመልከቻው ጋር ግንባታው በሚካሄድበት ቦታ ላይ ያለውን መብት የሚያሳይ ማስረጃ እና የግንባታ ፈቃድ ማያያዝ ይኖርበታል፡፡<br><br>፫/ በማሽነሪ ተከላ ምዕራፍ፡<br><br>ሀ) ድርጅቱ ለማሺነሪ ተከላ የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጠው ለአንድ አመት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ አላማ የሚሰጥ የስራ ፈቃድ አይታደስም፡፡<br>ለ) ሆኖም ተከላው ያልተጠናቀቀው የድርጅቱ ባልሆኑ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ከሆነ፡ ወይም ውስብስብ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ያካተተ ፕሮጀክት በመሆኑ ምክንያት መሆኑ ከታወቀ፡ አሊያም ድርጅቱ እጅግ ከፍተኛ ካፒታል ያፈሰሰ ተቋም የሆነ እንደሆነ ፈቃዱ ለተጨማሪ አመት ሊታደስ ይችላል፡፡<br>ሐ) ድርጅቱ ከስር በአንቀፅ ፰ ላይ ከተመለከቱ ሰነዶች በተጨማሪ | **6. <u>PROCEDURE TO DETERMINE THE NUMBER OF EXPATS EMPLOYED IN NON-MANAGEMENT POSITIONS</u>**<br><br>1/ Any investor may take out work permit and engage expats in his enterprise during construction phase, for machinery installation, auditing and accounting works, supervision, commissioning or testing, or as supervisors, trainers, maintenance, and in other technical roles only as per the procedures provided herein below.<br><br>2/ Project Construction Phase<br><br>a) Excluding the Project Manager and Deputy Project Manager, the number of expats employed by an enterprise during project construction phase shall not exceed 10% of the total number of Ethiopians employed and holding permanent project positions.<br><br>b) The Commission may decide to increase the threshold to up to 15% during the construction phase if the enterprise engages in expansion or upgrading by reinvesting its profit or other capital.<br>c) In addition to documents listed under Article 8, the enterprise shall submit, along with the application, proof supporting its entitlement over the construction site and present a construction permit.<br><br>3/ Machinery Installation Phase<br><br>a)The work permit issued to expats engaged in machinery installation shall be valid only for one year. Such work permit shall not be renewed.<br>b) However, the work permit may be renewed for additional year if the installation was delayed for reasons that were beyond the control of the |

ከማመልከቻው ጋር የማሽነሪውን መጫን ወይም ሀገር ውስጥ መግባት የሚያመለክት ሰነድ ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

፬/ በኮሚሽኒንግ ምዕራፍ፡

ሀ) ድርጅቱ ለዚህ አላማ የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጠው ለአንድ አመት ጊዜ ብቻ ነው፡፡
ለ) በዚህ መልክ የሚሰጥ የስራ ፈቃድ አይታደስም፡፡
ሐ) ድርጅቱ ከስር በአንቀፅ ፰ ላይ ከተመለከቱ ሰነዶች በተጨማሪ ከማመልከቻው ጋር ለሙከራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ሀገር ውስጥ መግባት/መገኘት ወይም ከውጭ አገር መጫን የሚያመለክት ሰነድ ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

፭/ በትግበራ (ኦፐሬሽን) ምዕራፍ፡

ሀ) የማኔጅመንት አባላትን ሳይጨምር ድርጅቱ የሚቀጥራቸው አጠቃላይ የውጭ አገር ሰራተኞች ቁጥር ከኢትዮጵያውያን ተቀጣሪዎች ቁጥር አንፃር ሲታይ ከ፲ በመቶ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡
ለ) ሆኖም እጅግ ከፍተኛ የሰው ሃይል በሚጠቀሙ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚቀጠሩ የውጭ አገር ሰራተኞችን ቁጥር በተለየ ሁኔታ እስከ ፲፪ በመቶ ከፍ እንዲል ኮሚሽኑ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
ሐ) በስራ ዘርፋቸው ልዩ ባህሪ ምክንያት ከፍተኛ የሰው ሃይል ቁጥር ስምሪትን በማይፈልጉ - የከፍተኛ ቴክኖሎጂ (high-tech) ኢንቨስትመንቶች፤ የአማካሪ (consultancy) ስራዎች፤ እና ከፍተኛ ሙያዊ እውቀት በሚሹ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች ላይ - በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፭(ሀ) እና ፭(ለ) ላይ የተመለከቱ ገደቦች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ኮሚሽኑ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊወስን ይችላል፡፡
መ) ይህ መመሪያ በወጣበት ጊዜ በንዑስ አንቀፅ ፭(ሀ) ላይ ከተመለከተው ከፍተኛ ጣሪያ በላይ የውጭ አገር ሰራተኞችን ቀጥረው የሚያሰሩ ድርጅቶች ግልፅ የድርጊት መርሀ-ግብር በማውጣት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከዚህ መመሪያ ጋር ወደሚስማማ አሰራር የመምጣት ግዴታ አለባቸው፡፡

፮ / ለጥገና፤ መሳሪያዎች እድሳት፤ ስልጠና እና ኦዲት ስራ፡

ሀ) ድርጅቱ ቋሚ ወይም ቀጣይነት ለሌላቸው የማሺነሪ ጥገና፤ እድሳት፤ ሱፐርቪዥን፤ ስልጠና፤ ኦዲትና ሂሳብ ሥራ እና ተመሳሳይ ኣላማዎች የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ሰራተኞች

enterprise and are not attributable to it, or the project entailed a high level and complex technology, or if the company has invested huge capital.
c) In addition to documents listed under Article 8, the enterprise shall submit, along with the application, documents supporting shipment or importation of the machinery into the country.

4/ Commissioning Phase

a) The work permit issued to expats employed by an enterprise for this purpose shall be valid for only one year.
b) A work permit issued in this manner shall not be renewed.
c) In addition to documents listed under Article 8, the enterprise shall submit, along with the application, proof showing the importation or local availability, or shipment of inputs required for commissioning.

5/ Implementation/Operation Phase

a) Excluding management members, the number of expats employed in the enterprise shall not exceed 10% of the total number of Ethiopian employees.
b) The Commission may however decide, based on study, to raise the threshold to up to 12% to affect investment sectors that require exceptionally high number of manpower.
c) Based on a study, the Commission may decide not to operationalize the restrictions provided under sub-articles 5(a) and 5(b) of this Article to investments, including high-tech investments, consultancy investments, and high-skill agricultural investments, which, because of their unique nature, do not require intensive engagement of labor force.
d) Enterprises that, at the time of the coming into force of this Directive, have employed expats above

| | |
|---|---|
| አንዴ የሚሰጠው የስራ ፈቃድ የሚቆየው ለሶስት ወር ጊዜ ብቻ ነው፡፡<br>ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፮(ሀ) መሰረት ለሶስት ወር የጸና የስራ ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ስራውን ባንድ ጊዜ እና በተከታታይ አሊያም በተለያየ ጊዜ እና በመመላለስ ለማከናወን አይከለከልም፡፡<br>ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፮(ሀ) መሰረት የሚሰጥ የስራ ፈቃድ አይታደስም፡፡ ሆኖም ስራው ያልተጠናቀቀው የድርጅቱ ባልሆኑ እና ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሳቢያ መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ ፈቃዱ ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ሊታደስ ይችላል፡፡<br>መ) ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የኦፐሬሽን ሂደቶቹ በመታወካቸው የማሺነሪ ጥገና ወይም እድሳት ስራ ማካሄድ ሲያስፈልገው በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እስከ ሁለት ጊዜ የስራ ፈቃድ እንዲሰጥለት ወይም ቀደም ሲል የተሰጠ ፈቃድ እንዲታደስለት መጠየቅ ይችላል፡፡ | the threshold provided under sub-article 5(a) shall prepare a clear action plan and conform with requirements of this Directive within one year.<br>6/ Repair, Maintenance, Training and Audit Works<br>a) A work permit issued for expats employed in temporary works including machinery repair, maintenance, supervision, training, audit and accountancy, and similar positions shall be valid for only three months.<br>b) An employee issued a three-month work permit in accordance with sub-article 6(a) of this Article may perform his work in one round and succession or at different times and intervals.<br>c) A work permit issued in this manner shall not be renewed. However, the permit may be renewed for one more term if it is proven that the work was not completed due to force majeure reasons not attributable to the enterprise.<br>d) Notwithstanding the above provision, an enterprise may request for the issuance of new work permit or renewal of an existing work permit up to two times in a given year when the operation of the company is disrupted due to requirements of machinery maintenance or renovation. |
| **፯. <u>ስለ ሥራ ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ እና የስራ ፈቃድ አጠቃቀም</u>**<br>፩/ በአንቀጽ ፭ እና ፮ መሰረት ለማኔጅመንትም ሆነ ከዚህ ውጭ ላሉ መደቦች የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው አሰሪ ድርጅት የውጭ አገር ዜግነት ያለው ሰራተኛ የስራ ፈቃድ ተሰጥቶት እንዲቀጠር ሲጠይቅ ብቻ ነው፡፡<br>፪/ ማንኛውም ቀጣሪ ድርጅት የውጭ አገር ዜጋን ለመቅጠር የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገው የማመልከቻ ቅጽ የሚጠይቀውን መረጃ በማሟላት ነው፡፡<br>፫/ በአንቀጽ ፭ እና ፮ መሰረት መሰረት የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ | **7. <u>SUBMISSION OF WORK PERMIT APPLICATION AND USE OF WORK PERMIT</u>**<br>1/ A work permit may be issued for management or other positions in accordance with Article 5 and 6 only based on a request made by an enterprise for employment of the expat.<br>2/ Any employer may request to obtain work permit for expat employee by filling out the information required in the application form annexed to this Directive.<br>3/ A work permit issued in accordance with Article 5 |

| | |
|---|---|
| የሚያገለግለው ፈቃዱን በጠየቀው ቀጣሪ ድርጅት ውስጥ ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መደብ ላይ ብቻ ለመሥራት ነው፡፡<br>፬/ ፈቃድ ከተሰጠበት የስራ መደብ ውጭ ተመሳሳይ ወይም ልዩነት ባለው ማናቸውም ሌላ የድርጅቱ ወይም የሌላ ድርጅት የስራ መደብ ላይ መስራት ወይም ተደራቢ አገልግሎት መስጠት በፍፁም የተከለከለ ነው፡፡<br>፭/ የውጭ አገር ዜጋ ፈቃዱን ካገኘበት የስራ መደብ ውጪ ሌላ የስራ ሀላፊነት: የእድገት: የዝውውር ወይም የቅጥር እድል ያጋጠመው እንደሆነ በአዲሱ የስራ መደብ መሰማራት የሚችለው አዲስ ማመልከቻ ቀርቦ የስራ ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው፡፡<br>፮/ የውጭ አገር ዜጋ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፭ መሰረት በአዲስ የስራ እድል ተጠቃሚ ለመሆን የሚሞላውን የማመልከቻ ቅጽ ከአገር ሳይወጣ ለኮሚሽኑ ማቅረብ እና አዲስ የስራ ፈቃድ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡<br>፯/ አሠሪው ድርጅት የሚቀጥረው የውጭ አገር ሰራተኛ የሚመደበው በጤና፤ በትምህርት እና ተመሳሳይነት ባላቸው ልዩ ሙያዊ ብቃትን በሚጠይቁ የስራ መደቦች ላይ ከሆነ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና በውጭ ሀገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ወይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የትምህርት፤ የሙያ ፈቃድ እና የልምድ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ | and 6 shall only be valid for providing service in the position applied for and within the requesting enterprise.<br>4/ Working in any position similar or different to the post for which a work permit is issued or engaging in supplementary works within or outside of the employing enterprise is absolutely prohibited.<br>5/ An expat can work in any new position he may be assigned, promoted to, transferred, or where he receives another job offer only upon submission of an application and issuance of a new work permit.<br>6/ An expat who intends to benefit from new work opportunities depicted under sub-article 5 of this article may submit application to the Commission and receive decision on a new work permit without having to leave the country.<br>7/ Where the expat employee is to be hired in health, educational and other similar sectors that require special professional skill, the employer enterprise must submit a competency certificate issued by the concerned government office, and academic credential, professional license and certificate of service authenticated by Ethiopian embassy abroad or the Ministry of Foreign Affairs. |
| **፰ . <u>አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ያለባቸው መሥፈርቶች</u>**<br>ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ለሚቀጥረው የውጭ አገር ዜጋ አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚከተሉትን ሰነዶች እና ማስረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>፩/ የተሞላ የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ፤<br>፪/ የተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የግል ታሪክ መግለጫ፤<br>፫/ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም የተረጋገጠ የውጭ አገር ዜጋው የትምህርት፤ የሙያ ብቃት እና የሥራ ልምድ ማስረጃ (ኦሪጅናል እና ኮፒ)፤<br>፬/ የውጭ አገር ዜጋው ከሦስት ወራት ያላነሰ ጊዜ ያለው ሕጋዊ ፓስፖርት፤<br>፭/ የፓስፖርት መጠን ያላቸው የውጭ አገር ዜጋው አራት ጉርድ | **8. <u>REQUIREMENTS TO OBTAIN A NEW WORK PERMIT</u>**<br>Any foreign investor applying for new work permit shall submit the following documents.<br>1/ duly completed application form;<br>2/ description of personal profile of the foreign employee;<br>3/ academic credentials, professional license or certificate of competence and certificate of service of the foreigner authenticated by a competent government body (original and copy);<br>4/ passport of the foreigner valid for not less than three months; |

| | |
|---|---|
| ፎቶግራፎች፤<br>፮/ እንደአግባብነቱ ጊዜው ያላለፈበት የሥራ ቪዛ (WV) ወይም ቢዝነስ ቪዛ (BV)፡ ወይም ጊዜው ያላለፈበት የስራ ፈቃድ፤<br>፯/ የውጭ አገር ዜጋው በጤና፤ በትምህርት ወይም መሰል ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤ በውጭ ሀገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ወይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የትምህርት፤ የሙያ ፈቃድ እና የልምድ ማስረጃዎች፤ የድጋፍ ደብዳቤ፤<br>፰/ የውጭ አገር ዜጋው ከአሠሪው ጋር የገባው የሥራ ቅጥር ውል፤<br>፱/ እንደአግባብነቱ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃድ፤<br>፲/ በሕግ የተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፤<br>፲፩ / የውጭ ባለሙያው ከተቀጠረ በኋላ ተግባራዊ የሚደረግ የተተኪ ኢትዮጵያዊ ቅጥር እና ምደባ ማስረጃ፤<br>፲፪/ ቀጣሪው ድርጅት ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ስለሚሰጠው ስልጠና እና ዕውቀት ሽግግር ያዘጋጀው ፕሮግራም፤ | 5/ four passport size photographs of the foreigner;<br>6/ as appropriate, valid work visa (WV), or business visa (BV), or work permit;<br>7/ if the expat employee engages in health, education or similar sectors, certificate of competence approved by the relevant government office; educational documents, professional license and certificate of service authenticated by an Ethiopian embassy abroad or the Ministry of Foreign Affairs; and support letter;<br>8/ employment contract between the expat and the enterprise;<br>9/ as appropriate, investment permit or business license;<br>10/ receipt showing payment of service charge determined by law;<br>11/ proof evidencing employment of Ethiopian replacement and assignment - to be operationalized after hiring the expat;<br>12/ training and knowledge transfer program organized by the enterprise - to be offered to Ethiopian replacement employees; |
| **ክፍል ፫**<br>**ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ስለሚሰጥ ስልጠና እና የእውቀት እና ክህሎት ሽግግር** | **PART 3**<br>**TRAINING AND KNOWLEDGE AND SKILLS TRANSFER OFFERED TO ETHIOPIAN REPLACEMENTS** |
| **፱. <u>ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ስለሚሰጥ ስልጠና እና የአተካክ ስርዓት</u>**<br>፩/ በማኔጅመንት እና ቀጣይነት በሌላቸው እንደ መሣሪያ ተከላ፣ ጥገና፣ እድሳት፤ ስልጠና፣ ሱፐርቪዥን፣ ኦዲት እና ሂሳብ ሥራዎች ላይ ከሚቀጠሩ በስተቀር በሌሎች የሥራ መደቦች ላይ ድርጅቱ የውጭ አገር ዜጋን ከመቅጠሩ በፊት የስራ መደቡ ወይም ዘርፉ በሚፈልገው ደረጃ ተመሳሳይ ሙያ ወይም ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ ጥረት ማድረግ አለበት። | **9. <u>PROVISION OF TRAINING TO ETHIOPIAN REPLACEMENTS AND PROCEDURE FOR REPLACEMENT</u>**<br>1/ Except for management and impermanent positions including machinery installation, maintenance, renovation, training, supervision, and audit and accountancy, an enterprise shall, for all other positions, exercise it best endeavor to explore the availability or otherwise of Ethiopians |

| | |
|---|---|
| ፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሀ አንቀፅ መሠረት የውጭ ዜጎችን የሚቀጥር ድርጅት ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊው የስራ ላይ ስልጠና እንዲዘጋጅ እና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ አገር ሠራተኞችን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ | possessing similar professional competence or experience required by the position or sector - prior to hiring any expat.<br>2/ Without prejudice to the stipulation of sub-article 1 of this Article, an enterprise hiring expats is obliged to set up and provide on-the-job training and replace expats with Ethiopians within a defined period of time. |
| **፲. <u>ስለስልጠናው ዓይነት እና የክትትል ስርዓት</u>**<br>፩/ ቀጣሪው ድርጅት ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ስለሚሰጠው ስልጠና እና ዕውቀት ሽግግር የሚያዘጋጀው ፕሮግራም እና ሪፖርት - እንደአግባብነቱ የውጭ ተቀጣሪዎች ስለሚተኩበት የጊዜ ገደብ፤ የሥልጠናዎቹን ዓይነትና መርሃ-ግብር፤ እንዲሁም በመርሃ-ግብሩ መሠረት የሚሰጡ/የተሰጡ ሥልጠናዎች የሩብ ዓመት የአፈጻጸም ዝርዝር የሚይዝ መሆን አለበት፡፡<br>፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በአሠሪው የሚቀርብ የፕሮግራም መግለጫ እና ሪፖርት እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበት፤<br>ሀ) የውጭ አገር ዜጋው ሙሉ ስም እና የተቀጠረበት የሙያ መስክ፣<br>ለ) የሥራ ላይ ሥልጠና የሚሰጣቸው ኢትዮጵያዊያን ሙሉ ስም፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የተቀጠሩበት የሙያ መስክ እና አድራሻ፣<br>ሐ) የሚሰጠው የሥራ ላይ ሥልጠና ዓይነትና የሚወስደው ጊዜ፣<br>መ) በተተኪነት የሚታሰቡት ኢትዮጵያዊያን ሠልጣኞች ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ያልቀሰሙ እንደሆነ ለዚህ ማብራሪያ፣<br>፫/ በቀጣሪው የሚቀርብ የመጀመሪያ ዙር የፕሮግራም መግለጫ እጅግ ቢዘገይ የውጭ አገር ሰራተኛው በተቀጠረ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡<br>፬/ የስልጠና እና እውቀት/ክህሎት ሽግግር ስራው ከተጀመረ በኋላ አሰሪው የመርሀ-ግብሩን የየሩብ አመት አፈፃፀም ዝርዝር ሪፖርት በየወቅቱ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ ሪፖርቱ ኮሚሽኑ አስቀድሞ በሚያወጣው እና በሚልከው ዝርዝር የጊዜ እና ክትትል ሰሌዳ መሰረት ይቀርባል፡፡<br>፭/ ለኢትዮጵያዊያን የሚሰጡ የስራ ላይ ሥልጠናዎች አፈጻጸም እና ውጤታማነትን አስመልክቶ ኮሚሽኑ በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ | **10. <u>Type of Training and Supervision Procedure</u>**<br>1/ The report and training program to be prepared by the enterprise on training and knowledge transfer shall, as appropriate, consist of timeline for the replacement of expat employees, nature and schedule of trainings, and quarterly performance report of trainings offered or due to be offered as per the schedule.<br>2/ The program description and report submitted in accordance with sub-article 1 of this Article shall consist of the following details:<br>a) full name and professional position of the foreigner;<br>b) full name, level of education, profession, and address of Ethiopians who shall receive on-the-job training;<br>c) type of training and timeframe for its completion;<br>d) where replacement Ethiopian trainees failed to acquire knowledge and skills in required levels and within the stipulated timeframe, an explanation to such effect;<br>3/ The first-round training program prepared by the enterprise shall, at the latest, be presented within one week from the date of employment of the expat.<br>4/ The enterprise shall periodically submit detailed quarterly performance report after commencement of training, knowledge and skills transfer program. |

| | |
|---|---|
| የመስክ ክትትል እና ቁጥጥር ያደረጋል፡፡ | The report shall be submitted as per a detailed supervisory timeframe pre-arranged and communicated by the Commission.<br>5/ The Commission shall conduct field monitoring and supervision every three months to assess the implementation and effectiveness of on-the-job trainings offered to Ethiopians. |
| **<u>፲፩. የሥራ ፈቃድ የጊዜ ገደብ</u>**<br>፩/ በአንቀጽ ፭ እና ፮ ላይ በተለየ መልኩ ከተቀመጡ የጊዜ ገደብ ድንጋጌዎች ውጭ ባሉ ሁኔታዎች በአንድ የሥራ መደብ ላይ ለመሥራት የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለአንድ አመት ነው፡፡<br>፪/ የስራ ፈቃድ ድርጅቱ እንደአግባብነቱ ተተኪ ኢትዮጵያውያንን በማሰልጠን ረገድ የወሰደውን ተጨባጭ እርምጃ መሠረት በማድረግ በየአመቱ ከሶስት አመታት ላልበለጠ አጠቃላይ ጊዜ ይታደሳል፡፡<br>፫/ የሥራ ፈቃድ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋን ቀጥሮ ለማሰራት ባመለከተው መሰረት ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡<br>፬/ የስራ ፈቃድ ማመልከቻው የዘገየው በድርጅቱ ወይም በባለሙያው ጥፋት ካልሆነ በቀር የውጭ አገር ዜጋው አገር ውስጥ ከገባ ከ፴ የሥራ ቀናት በኋላ የሚቀርብ የሥራ ፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡<br>፭/ ልዩ በሆኑ አስገዳጅ ወይም አስፈላጊ ሁኔታዎች ምክንያት - ቢያንስ ፵ ሚሊዮን ዶላር የኢንቨስትመንት ካፒታል ስላፈሰሱ ወይም ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ ሰራተኞች የቀጠሩ በመሆኑ - በኮሚሽኑ ልዩ ፈቃድ በሌላ መልኩ ካልተወሰነ በቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ ላይ የተመለከተው የሦስት ዓመት ከፍተኛ የጊዜ ገደብ አይራዘምም፡፡<br>፮/ እንዲሁም የድርጅቱ ባልሆኑ ምክንያቶች የእውቀት ወይም ክህሎት ሽግግር መርሃ-ግብሩ በተፈለገው ደረጃ አለመከናወኑ በማያሻማ ሁኔታ በማስረጃ በመረጋገጡ ወይም የሰለጠኑት ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ፈቃድ ከድርጅቱ በመልቀቃቸው ወይም የስራ ውሉ በሰልጣኝ ሰራተኛው ጥፋት በመቋረጡ ምክንያት ካልሆነ በቀር በነዚሁ መደቦች ላይ ሌላ የውጭ አገር ዜጋ መቅጠር አይፈቀድም፡፡ | **11. <u>VALIDITY OF WORK PERMIT</u>**<br>1/ Apart from special timeframes provided for under Article 5 and 6, a work permit issued in relation to a particular position shall be valid for one year.<br>2/ A work permit may be renewed annually for not more than three years taking into account the actual measures undertaken by the enterprise to train Ethiopian replacements.<br>3/ The validity period of work permit commences to run from the date of issuance of the work permit following submission of application by the enterprise.<br>4/ Unless it is proven that the submission of work permit application was delayed for a fault not attributable to the enterprise or expat, an application for work permit submitted more than 30 days after the expat's arrival in Ethiopia shall not be accepted.<br>5/ Apart from exemptions which may be dispensed by the Commission in compelling or necessary conditions, including in cases where an enterprise has invested a capital of at least 40 million USD or hired more than one thousand five hundred employees, the three years maximum period specified under sub-article 2 of this Article shall not be extended.<br>6/ An enterprise cannot assign a new expat employee to such positions on which a foreigner had previously served for three years; however, an |

| | |
|---|---|
| | enterprise may be allowed to do so when it is unequivocally demonstrated through evidence that the transfer of knowledge and skill was not properly implemented for reasons not attributable to the enterprise, or because the trained Ethiopians left the enterprise through own will, or the contract of employment was terminated through the fault of the trainee employee. |
| **፲፪. የስራ ፈቃድ እድሳት ሁኔታዎች**<br><br>፩/ የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ የሚስተናገደው አሰሪው እንዲያሟላ የሚጠበቀው የኢትዮጵያውያን ተተኪዎች ስልጠና አፈጻጸም በተገቢ ደረጃ መወጣቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡<br>፪/ በአሰሪው በኩል፡<br>ሀ) በዚህ ረገድ የወሰደው እርምጃ በቂ ሆኖ ካልተገኘ፤ ወይም<br>ለ) ለችግሮቹ ያቀረበው ምክንያት አሳማኝ ካልሆነ፤<br>ሐ) ከተተኪ ሰራተኞች ወቅታዊ ዝግጅት አንፃር ኢትዮጵያዊው ተተኪ የውጭ ዜጋውን የሥራ መደብ መሸፈን የሚችል መሆኑ በኮሚሽኑ ከታመነ፤<br>መ) አሊያም ተመሳሳይ ችሎታ ወይም ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች በገበያ ላይ ስለመኖራቸው በግልፅ የሚታወቅ በመሆኑ የውጭ አገር ዜጋው ለተቀጠረበት ሥራ አስፈላጊ አለመሆኑ ኮሚሽኑ ካመነ፡<br>የሥራ ፈቃዱ አይታደስም፡፡<br>፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፪ ከተመለከተው ውጭ ባሉ ሁኔታዎች የውጭ አገር ዜጋው ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና የተቀጠረበት ሥራ ቀጣይ እና አስፈላጊ መሆኑ በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ የስራ ፈቃድ ይታደሳል፡፡ | **12. CONDITIONS FOR RENEWAL OF WORK PERMIT**<br><br>1/ An application for renewal of a work permit may be approved only if it is proven that the enterprise has executed the training of Ethiopian replacements appropriately.<br>2/ If the employer:<br>a) has not taken sufficient measure in this regard, or<br>b) fails to provide convincing reason for its failure, or<br>c) if, considering the preparatory works undertaken, the Commission is convinced the Ethiopian replacement can take over the position filled by the expat employee, or<br>d) if it is openly known that Ethiopians possessing comparable knowledge or experience are available in the job market - convincing the Commission about the irrelevance of the expat employee for the position assigned,<br>the work permit shall not be renewed.<br>3/ Without prejudice to the circumstances specified under sub-article 2 of this Article, a work permit may be renewed when it is proved by the Commission that the expat is relevant for the position and that the particular work is of a continuous nature. |
| **፲፫. የሥራ ፈቃድ ለማደስ መሟላት ያለባቸው ሰነዶች**<br><br>፩/ ማንኛውም አሠሪ የሥራ ፈቃድ ለማደስ የሥራ ፈቃድ ጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን | **13. DOCUMENTS REQUIRED FOR RENEWAL OF WORK PERMIT**<br><br>1/ An employer shall submit its application for |

| | |
|---|---|
| በማሟላት ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>ሀ) የተሞላ የውጭ አገር ዜጋው የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻ፤<br>ለ) የውጭ አገር ዜጋው ከሦስት ወራት ያላነሰ ጊዜ ያለው ፓስፖርት፤<br>ሐ) ከኮሚሽኑ ወይም ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ደብተር፤<br>መ) እንደአግባብነቱ የመኖሪያ ፈቃድ፣<br>ሠ) የውጭ አገር ዜጋው በጤና፡ በትምህርት ወይም መሰል ዘርፍ ሥራ ላይ የሚሠማራ ከሆነ እንደአግባብነቱ ከጤና፡ ከትምህርት ወይም ሌሎች ተቋማት የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤<br>ረ) የውጭ አገር ዜጋው ከአሠሪው ጋር የገባው የሥራ ቅጥር ውል፤<br>ሰ) የተተኪ ኢትዮጵያዊያንን የዕውቀት ሽግግር ሁኔታን የሚገልጽ ሙሉ አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት፤<br>ሸ) በሕግ የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፤<br>ቀ) እንደአግባብነቱ የታደሰ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃድ፤<br>፪/ አሠሪው የውጭ አገር ዜጋውን የሥራ ፈቃድ በወቅቱ ሳያሳድስ የቀረ እንደሆነ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃበት በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ለመጀመሪያው ወር የዕድሳት ክፍያውን ሃምሣ በመቶ (፶%)፣ ለሁለተኛው ወር ሰባ አምስት በመቶ (፸፭%)፣ እና ለሦስተኛው ወር መቶ በመቶ (፻%) ቅጣት በተጨማሪ በመክፈል የሥራ ፈቃዱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡ | renewal of a work permit to the Commission together with the following documents within one month before the expiry of the permit.<br>a) duly completed application of the expat;<br>b) the expat's passport valid for at least three months;<br>c) work permit book issued by the Commission or the Ministry of Labor and Social Affairs before the coming into force of this Directive;<br>d) residence permit where appropriate;<br>e) a support letter issued by health, education, or related institutions if the expat engages in health, education or other related professions;<br>f) an employment contract concluded between the employee and employer;<br>g) a complete annual performance report providing information on the condition of transfer of knowledge to Ethiopian replacements;<br>h) receipt showing service fee charge;<br>i) a renewed investment permit or business license, as appropriate;<br>2/ If the employer fails to renew the expat work permit in time, it shall pay 50% additional penalty fee for the first month's renewal after expiry of the work permit, 75% additional penalty fee for the second month, and 100% additional penalty fee for the third month and seek renewal of the work permit. |
| **፲፬. <u>የሥራ ፈቃድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ</u>**<br>፩/ የሥራ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ይሠረዛል፡፡<br>ሀ) የሚታደስ ካልሆነ በቀር የውጭ አገር ዜጋው የተሰጠው የሥራ ፈቃድ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ፤<br>ለ) የውጭ አገር ዜጋው የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ ጊዜ ባይጨርስም ለሥራው አስፈላጊ አለመሆኑ በአሠሪው ወይም በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ፤<br>ሐ) የውጭ አገር ዜጋው ፈቃድ በተጠየቀለትና በተፈቀደለት ሥራ | **14. <u>CONDITIONS FOR REVOCATION OF WORK PERMIT</u>**<br>1/ A work permit shall be revoked for the following reasons.<br>a) on expiry of the work permit period, unless there is intention to renew;<br>b) when it is ascertained by the employer or the Commission that the expat is no longer required for |

| | |
|---|---|
| ላይ ሳይሆን ለሌላ አሰሪ ሲሰራ ወይም በተደራቢ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲገኝ፤<br>መ) የውጭ አገር ዜጋው ይሰራው የነበረው ሥራ ሲያልቅ፡ ወይም የማያስፈልግ ሲሆን ወይም ድርጅቱ ሲዘጋ፤<br>ሠ) የሥራ ፈቃድ ከሦስት ወር በላይ ለሆነ ጊዜ ሳይታደስ ሲቀር፤<br>ረ) የውጭ አገር ዜጋው በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ለአገሪቱ ደህንነት አስጊ መሆኑ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ሲታመንበት፤<br>ሰ) የውጭ አገር ዜጋው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ፤<br>ሸ) የሥራ ፈቃዱ በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የተሰጠ ከሆነ፤<br>ቀ) በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ የአሠሪና የሠራተኛ ግዴታዎች ሳይፈጸሙ ሲቀሩ፡፡<br>፪/ የሥራ ፈቃድ ሲሰረዝ አሠሪው የሥራ ፈቃድ ደብተሩን ለኮሚሽኑ መመለስ አለበት፡፡ | the job although the work permit remains valid;<br>c) when the expat is found working for a different employer or is engaged in supplementary work different from the approved stream;<br>d) upon completion of the work undertaken by the expat, or the when the job is no longer needed, or when the enterprise closes;<br>e) failure to renew a work permit for more than three months;<br>f) when it is held by the relevant government organ that the expat's continued residence in Ethiopia poses threat to national security;<br>g) when the expat resigns from his job;<br>h) when the work permit was issued based on wrong information;<br>i) failure to comply with employer and employee obligations prescribed under this Directive;<br>2/ Upon revocation, the employer shall return the work permit book to the Commission. |
| **፲፭. <u>የአሠሪ ግዴታዎች</u>**<br>በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፮/፳፻፲፩ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አሠሪው የሚከተሉት ተጨማሪ ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡<br>፩/ የሥራ ፈቃድ የተሰጠውን የውጭ ዜጋ በተፈቀደለት የሙያ መስክ እና መደብ ላይ ብቻ የማሰራት፤<br>፪/ ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋ ከ፭ የስራ ቀናት በላይ ለሆነ ጊዜ ከሥራ ቦታ የተሰወረ እንደሆነ መጥፋቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ በጽሁፍ የማሳወቅ፤<br>፫/ ኮሚሽኑ የውጭ አገር ዜጋው በአካል እንዲቀርብለት ሲጠይቅ አስፈላጊውን የመፈፀም፤<br>፬/ አሠሪው ድርጅት የውጭ አገር ዜጋ ሰራተኛውን አገልግሎት የማይፈልግ ሆኖ የሥራ ውሉን ሲያቋርጥ የሥራ ውሉን ባቋረጠ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለኮሚሽኑ በጽሁፍ የማሳወቅ እና የሥራ ፈቃድ ደብተሩን የመመለስ፤<br>፭/ ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋው የሚሠራበትን የሥራ ቦታ ከቀየረ አዲሱ አድራሻ በተቀየረ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ | **15. <u>EMPLOYER'S OBLIGATIONS</u>**<br>Without prejudice to provisions of the Labor Proclamation No.1156/2019, the employer shall have the following additional duties.<br>1/ To assign the expat only in the authorized professional line and work position.<br>2/ To notify the Commission in writing, within 5 working days from the date of knowledge of the disappearance, about the leaving of the expat from the place of work.<br>3/ To implement accordingly when the Commission requests physical appearance of the expat.<br>4/ To notify the Commission in writing within 5 working days of the termination and return the work permit book when the contract of employment is ended.<br>5/ In case of a change of workplace, to notify the |

| | |
|---|---|
| የማሳወቅ፤<br>፮/ የውጭ አገር ዜጋውን የመኖሪያ አድራሻ መዝግቦ በመያዝ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የማሳየት/የማቅረብ፤<br>፯/ ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋው ከትራፊክ ደንብ መተላለፍ ውጭ በወንጀል የሚያስጠይቁ የአገሪቱ ሕጎችን መጣሱ በበቂና አሳማኝ መንገድ ሲታወቅ የሥራ ፈቃዱን ለኮሚሽኑ አቅርቦ እንዲሰረዝ የማድረግ፤<br>፰/ የስራ ፈቃድ የሌለውን የውጭ አገር ዜጋ በማናቸውም ሁኔታ ሥራ ላይ ያለማሰማራት፤<br>፱/ ተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋውን በሕገወጥ ሥራዎች ወይም ለሞራል ተጻራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ ያለማሰማራት፤<br>፲/ ከተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጋ ሰራተኛው ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ተገቢው እውቀትና ክህሎት የሚተላለፍበትን ሁኔታ መፍጠርና በተጨባጭ ማረጋገጥ። | Commission about the new address of the expat employee within 5 working days after the change.<br>6/ To maintain residence address record of the expat and show the same whenever requested by the appropriate organ.<br>7/ To return the work permit and cause its cancellation when it is sufficiently and credibly demonstrated that the expat has violated the criminal laws of the country, excluding minor traffic offences.<br>8/ To refrain from deploying an expat who is not issued with work permit in any type of work.<br>9/ To refrain from deploying an expat in any unlawful works or immoral activities.<br>10/ To facilitate and concretely ascertain knowledge and skills transfer from expat employees to Ethiopian replacements. |
| **፲፮. <u>የተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ ግዴታዎች</u>**<br>በሀገሪቱ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፮/፪፻፲፩ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተቀጣሪው የውጭ አገር ዜጋ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል።<br>፩/ የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ በመያዝ በሥራ ገበታው ላይ የመገኘት፤<br>፪/ በሥራ ፈቃድ ደብተሩ ላይ ለተመለከተው አሠሪ ብቻ የመሥራት፤<br>፫/ በሥራ ፈቃድ ደብተሩ ላይ በተመዘገበው የሥራ መደብ/ሙያ ላይ ብቻ የመሰማራት፤<br>፬/ በሚሰጠው መርሀ-ግብር እና አሰራር መሰረት ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እውቀት እና ክህሎት የማስተላለፍ፣<br>፭/ በሕገወጥ ሥራዎች እና ለሞራል ተፃራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ አለመሰማራት፤<br>፮/ ወደ ኮሚሽኑ ቀርቦ ሪፖርት እንዲያደርግ ሲጠየቅ በወቅቱ መገኘት። | **16. <u>EXPAT EMPLOYEE'S OBLIGATIONS</u>**<br>Without prejudice to provisions of the Labor Proclamation No.1156/2019, the expat employee shall have the following obligations.<br>1/ To appear at a workplace in possession of the issued work permit;<br>2/ To work only for the employer specified in the work permit;<br>3/ To engage only in the position/profession registered in the work permit;<br>4/ To transfer standard knowledge and skill to Ethiopian replacements in accordance with the pre-arranged schedule and procedure;<br>5/ To refrain from engaging in illegal and immoral activities;<br>6/ To comply with the Commission's request for reporting; |
| **፲፯. <u>ጉዳይ አስፈፃሚ ስለመወከል</u>**<br>፩/ ማንኛውም አሠሪ ድርጅት የውጭ አገር ዜጎችን ቀጥሮ | **17. <u>APPOINTMENT OF LIAISON OFFICER</u>**<br>1/ An employer must appoint a liaison officer who |

| | |
|---|---|
| ለማሰራት የሚያቀርበውን የሥራ ፈቃድ ጥያቄ የሚያስፈጽም ሰው መወከል አለበት፡፡<br>፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በጽሑፍ የሚወከል ጉዳይ አስፈጻሚ፡-<br>ሀ) የድርጅቱ ሠራተኛ ከሆነ ከውክልና ደብዳቤ ጋር ሠራተኛነቱን የሚያረጋግጥ የድርጅት መታወቂያ እና የቀበሌ መታወቂያ/ፓስፖርት (ኦሪጅናል እና ፎቶ ኮፒ)፤<br>ለ) ሦስተኛ ወገን ከሆነ በኢፌዲሪ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ የተረጋገጠ ውክልና እና የቀበሌ መታወቂያ/ፓስፖርት ይዞ መቅረብ አለበት፡፡<br>፫/ ከላይ የተመለከተው ቢኖርም የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሥራ ሀላፊነቱን የሚያስረዳ ደብዳቤ በመያዝ የሥራ ፈቃድ ጥያቄውን ራሱ ሊያስፈጽም ይችላል፡፡ | facilitates services relating to work permit.<br>2/ When a liaison officer assigned in line with this Article:<br>a) is employee of the enterprise, he shall produce employment ID Card, in addition to a power of attorney and Kebele ID Card/Passport (original and copy);<br>b) is any other third party, he shall produce a power of attorney authenticated by the FDRE Documents Authentication and Registration Agency and a Kebele ID card/ Passport;<br>3/ Notwithstanding the above stipulation, a general manager of an enterprise can process the work permit request by himself, provided that he can adduce a letter proving his status in the enterprise. |
| **፲፰. <u>በተቀጣሪ የውጭ አገር ዜጎች ላይ ስለሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር</u>**<br><br>የውጭ አገር ዜጎችን ቅጥር አስመልክቶ በአዋጁ ላይ የተደነገጉትን፡ እንዲሁም አዋጁን መሠረት በማድረግ የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎችን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ኮሚሽኑ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ | **18. <u>MONITORING AND SUPERVISION OF EXPAT EMPLOYEES</u>**<br><br>The Commission shall engage in monitoring and supervisory activities to ensure the enforcement of provisions of the Proclamation, subsequently adopted Regulation, and Directives pertaining to expat employment. |
| **፲፱. <u>የሥራ ፈቃድ ደብተር ስለመተካት</u>**<br><br>፩/ የሥራ ፈቃድ ደብተር ሲጠፋ አሰሪው መጥፋቱን እንዳወቀ ወዲያውኑ የጠፋበትን ምክንያት የሚገልጽ በድርጅቱ የተፈረመ መግለጫ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡<br>፪/ አሠሪው በዚህ አንቀጽ ከተገለጸው በተጨማሪ የሥራ ፈቃድ ደብተር ለመጥፋቱ የፖሊስ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡<br>፫/ ኮሚሽኑ የቀረበለትን ማስረጃ በማረጋገጥ እና በሕግ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምትክ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ | **19. <u>REPLACEMENT OF WORK PERMIT</u>**<br><br>1/ When a work permit book is lost, the employer shall notify the Commission in writing about the occurrence of such incidence and cause of the loss immediately upon becoming aware of the incident.<br>2/ In addition to the stipulation herein above, the employer shall adduce a police statement evidencing loss of the work permit book.<br>3/ The Commission shall issue a replacement work permit after verifying the evidences adduced and receipt of payment of service fee charged under the law. |
| **፳. <u>የሥራ ፈቃድ ክሊራንስ</u>** | **20. <u>WORK PERMIT CLEARANCE</u>** |

| | |
|---|---|
| ፩/ ማንኛውም አሠሪ የሥራ ፈቃድ ላወጣለት የውጭ አገር ዜጋ ክሊራንስ የፈለገ እንደሆነ የሚከተሉትን አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>ሀ) ከቀጣሪው ድርጅት የሚቀርብ የተሞላ የክሊራንስ ማመልከቻ እና<br>ለ) የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ ደብተር ተመላሽ ማድረግ፡፡<br>፪/ ከላይ የተመለከተው ቢኖርም ቀጣሪው ድርጅት ከተዘጋ ወይም ሥራውን ካቆመ የውጭ አገር አገር ዜጋው ድርጅቱ ስለመዘጋቱ ወይም ሥራውን ስለማቆሙ ከሚመለከተው የኮሚሽኑ የስራ ክፍል ማስረጃ በማቅረብ ሲጠይቅ የሥራ ፈቃድ ክሊራንስ ሊሰጠው ይችላል፡፡<br>፫/ በዚህ አንቀጽ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀደም ብሎ የተሰጠው የሥራ ፈቃድ ጊዜው ካለፈ ከአንድ ወር በኋላ የሚቀርብ የክሊራንስ ጥያቄ የሥራ ፈቃዱ ያልታደሰበትን ጊዜ የሚሸፍን የእድሳት ክፍያን መጠን በመክፈል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ | 1/ Any employer seeking a clearance letter for his expat employee shall submit the following:<br>a) duly completed clearance application by the enterprise, and<br>b) return the work permit book<br>2/ Notwithstanding the above provision, an expat employee of an enterprise which is forced to close or halt its business may be issued clearance on producing proof from the Commission.<br>3/ Without prejudice to the above provision, a clearance request made one month after the expiry of the validity date of the work permit shall entail payment of renewal fee commensurate with the lapsed period. |
| **<u>፳፩</u>. <u>ስለ አገልግሎት ክፍያ</u>**<br>የውጭ አገር ዜጎችን ቀጥሮ ለማሰራት የሚፈልግ ማንኛውም አሠሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሥራ ፈቃድ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያን በተመለከተ ባወጣው ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፳፻፱ መሠረት የሚከተለውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም አለበት፤<br>፩/ አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማውጣት ብር ፳፻ (ሁለት ሺ ብር)፤<br>፪/ የሥራ ፈቃድ ለማሳደስ ብር ፲፭፻ (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር)፤<br>፫/ የሥራ ፈቃድ ደብተር ለመተካት ብር ፲፪፻ (አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር)፡፡ | **21. <u>SERVICE CHARGE</u>**<br>An enterprise who seeks to employ expat is required to pay service fee in accordance with the Council of Ministers Regulation No.394/2016 as provided below.<br>1/ issuance of new work permit ETB 2000.00 (Two Thousand Birr);<br>2/ renewal of work permit ETB 1500.00 (One Thousand Five Hundred Birr);<br>3/ replacement of work permit ETB 1200.00 (One Thousand Two Hundred Birr); |
| **ክፍል <u>፬</u>**<br>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** | **PART 4**<br>**MISCELLANEOUS PROVISIONS** |
| **<u>፳፪</u> . <u>ቅጣት</u>**<br>፩/ አሠሪው ድርጅት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ግዴታዎችና ሌሎች ኃላፊነቶች ካልተወጣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፮/፳፻፲፩ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ስለቅጣት የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡<br>፪/ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፮/፳፻፲፩ ስለቅጣት የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚሽኑ በዚህ | **22. <u>PENALTY</u>**<br>1/ An employer who violates duties and obligations stated in this Directive shall be punished pursuant to the Labor Proclamation No.1156/2019 and other relevant laws.<br>2/ Without prejudice to penalty provisions stated under the Labor Proclamation No.1156/2019, the |

| | |
|---|---|
| መመሪያ መሠረት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው የሚሰራ የውጭ አገር ዜጋ ተገቢ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል። | Commission shall take appropriate measures against expat employee who works without obtaining a work permit in accordance with this Directive. |
| **፳፫. <u>የመተግበር ግዴታ</u>**<br><br>ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት። | **23. <u>DUTY TO IMPLEMENT</u>**<br><br>Every person shall cooperate in the proper implementation of this Directive. |
| **፳፬. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**<br><br>፩/ በአንቀፅ ፫ ላይ ከተመለከቱ የኢንቨስትመንት ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በኮሚሽኑ ሆነ በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ የሥራ ፈቃዶች ቀጣይ አስተዳደር ጉዳይ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡<br>፪/ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ የሚታቀፉ እና አሁንም በጥቅም ላይ ያሉ የስራ ፈቃድ መዝገቦችን እና ደጋፊ የአሰራር ሶፍትዌሮችን ለኮሚሽኑ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ያስተላልፋል። | **24. <u>TRANSITORY PROVISIONS</u>**<br><br>1/ In relation to investments specified under Article 3, the administration of work permits issued by the Commission or the Ministry of Labor and Social Affairs prior to the issuance of this Directive to shall be governed by this Directive.<br>2/ The Ministry of Labor and Social Affairs shall transfer to the Commission all active work permit dossiers that fall under this Directive as well as other supporting software within six months period. |
| **፳፭ . <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**<br><br>ይህ መመሪያ በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ተመዝግቦ እና ቁጥር ተሰጥቶት በኮሚሽኑ ድህረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ጀምሮ የፀና ይሆናል። | **25. <u>EFFECTIVE DATE</u>**<br><br>This Directive shall enter into force on the date of its registration and numbering by Office of the Federal Attorney General and its posting on the Commission's website. |

**ሌሊሴ ነሜ**

**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን**

**ኮሚሽነር**

**Lelise Neme**
**Ethiopia Investment Commission**

**Commissioner**